**SIDAAMU DAGOOMU QOQQOWI MOOTIMMA AFFINI GAAZEEXA**

**የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት አፍኒ ጋዜጣ**

**SIDAAMA NATIONAL REGIONAL STATE AFFINI GAZETA**

5[kki] Diro Kiiro …

Hawassa, Badheessa 8/2017 M.D

Sidaamu Dagoomu Qoqqowu Mootimma Amaale Mini Allaalshi Hundaanni Fulinoho

በሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

5ኛ ዓመት ቁጥር …

ሀዋሳ መጋቢት ፰ ቀን ፳፻፲፯ ዓ.ም


**Amado**

**Wodhote Kiiro 48/ 2017**

**Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Latishshu Urrinshubba Qorqorshi Biilloonyi Biilloonyenna Loosu Qeecha Murate Fultino Wodho**

**WODHOTE KIIRO 48/2017**

**Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Latishshu Urrinshubba Qorqorshi Biilloonyi Biilloonyenna Loosu Qeecha Murate Fultino Wodho**

Qoqqowu giddo noorinna albillitte uurritanno latishshu uurrinshubba aana qoqqowu mootimma heedhannose annimmate qosso buuxisate dandiinanni gedenna latishshu urinshubbano tantanantino gafa ganate umosi dandiino qorqoranno jeefisiisaancho motimmate bisi biilloonyenna loosu qeecha seerunni muratenni latishshu uurrinshubba

**ማውጫ**

**ደንብ ቁጥር ፵፰/፳፻፲፯**

**የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣ ደንብ**

**ደንብ ቁጥር ፵፰/ ፳፻፲፯**

**የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣ ደንብ**

በክልሉ ውስጥ የነበሩና ወደፊት ሊቋቋሙ የሚችሉ የልማት ድርጅቶች ላይ የክልሉ መንግሥት የሚኖረውን ባለቤትነት መብት ለማረጋገጥ እንዲቻልና የልማት ድርጅቶቹም የተቋቋሙበትን አላማ በብቃት ለመወጣት እንዲችሉ ራሱን የቻለ ተቆጣጣሪ አስፈጻሚ የመንግሥት አካል ሥልጣንና ተግባር በመወሰን

konni bisira hundaano assa hasiissinohura;

Mootimmate latishshu uurrinshubba loosu wolapho afidhannonna loosinsa amuraate yannicha assitanno tantanonna amanyoote diriirsatenni, hojji kubbaniyubba ledo heewisantanni loosa dandiisiisannonsata ikkadimmate raga burqisatenni, uurritino mixo jeefo iillishshanno gede harunsonna qorqorsha assanno latishshu uurrinshubba biilloonyi biilloonyenna loosu qeecha faajjetenni mura hasiissinohura;

Woyyaawino Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Jeefisiisaano Bissa Uurrisatenna Biilloonyenna Loosu Qeecha Murate Fulino Lallawa Kiiro 32/2015 10 (13) aana uuynoonnisi biilloonyi garinni Qoqqowu Jeefisiisaanote Amaale Mini tenne wodho fushshino.

**GAFA MITE**

**<u>Xaphooma Woro</u>**

1. **<u>Harancho Umo</u>**

   Tenne wodho **"Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Mootimmate Latishshu Uurrinshubba Qorqorshi Biilloonyi Biilloonyenna Loosu Qeecha Murate Fultino Wodho 48/2017"** yine woshshinara dandiinanni.

2. **<u>Tiro</u>**

   Qaalu eo wole tiro uysiissanota ikka hoogguro tenne wodho giddo:-

   1. **"Mootimma"** yaa Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimmaati.

የልማት ድርጅቶቹ ተጠሪነት ለዚሁ አካል እንዲሆን ማድረግ በማስፈለጉ፤

የመንግሥት የልማት ድርጅቶች የአሰራር ነጻነት የሚያገኙበትንና ስርዓታቸውን ማዘመን የሚችሉበት ሥርዓት በመዘርጋት፤ ከግል ኩባንያዎች ጋር እየተወዳደሩ መስራት የሚያስችላቸዉን የብቃት አቅጣጫ በመቀየስ፤ የተቋቋሙበትን ዓላማ ከግብ እንዲያደርሱ ክትትል እና ቁጥጥር የሚያደርግ የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ሥልጣንና ተግባር በግልጽ መደንገግ በማስፈለጉ፤

የተሻሻለዉ የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት አስጻሚ አካላት ማቋቋም፣ ሥልጣንና ተግባር መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 32/2015 አንቀጽ 10 (13) በተሰጠው ሥልጣን መሠረት የክልሉ ርዕሰ መስዳድር ምክር ቤት ይህንን ደንብ አውጥቷል።

**ክፍል አንድ**

**<u>ጠቅላላ ድንጋጌ</u>**

1. **<u>አጭር ርዕስ</u>**

   ይህ ደንብ **"የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣ ደንብ ቁጥር ፵፰/፳፻፲፯"** ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **<u>ትርጓሜ</u>**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ዉስጥ:-

   1. **"መንግሥት"** ማለት የሲዳማ ብሔራዊ ክልል መንግሥት ነዉ።

2. **“Biilloonye”** yaa Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Moottimmate Latishshu Uurrinshubba Qorqorshi Biilloonyeeti.
3. **“Latishshu Uurrinshubba”** yaa latishshu uurrinshubba lallawi kiiro 28/2015 quwa 2(6) worrooni tiro wonshitanno latishshu uurrinsha woy akisyoone wo’munni wo’ma mootimma annimmatenni amaddino akisyoonete maamara woy akisyoone rooriiydi anga mootimma annimmatenni amaddino akisyoonete maamaraati.
4. **“Borde”** yaa latishshu uurrinsha looso aliidimmatenni massagganno gede uurritanno latishshu uurrinsha bordeeti.
5. **“Xaphooma Jiro”** yaa baalanka milli yaannokkinna milli yaanno jajja, gamba assinanni jiro, kiiranni womaashsha, baankete shallago, latishshu uurrinshubbata bisi-afiriweello jiro, owaantete baatooshshubbanna woloota asalubba xaphisanno.
6. **“Xaphooma Buuxantino Jiro”** yaa xaphooma jironni harancho yanna assale, seeda yanna asalenna wooloota asalubba xeinseenna afantanno jirooti.
7. **“Kaapitaale”** yaa mitte latishshu uurrinsha uurritanno yannaranna hakkuyi gedensaanni mootimmatenni gaammanni xaphooma buuxantino jiro gaammoonni yannara noose waagaati.

2. **“ባለሥልጣን”** ማለት የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ነው፡
3. **“የልማት ድርጅቶች”** ማለት በልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፳፰/፳፻፲፭ አንቀጽ 2(6) የተመለከተዉን ትርጓሜ የሚያሟላ የልማት ድርጅት ወይም አክሲዮኖቹ ሙሉ በሙሉ በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘ አክሲዮን ማህበር ወይም አክሲዮኖቹ በአብላጫዉ በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘ አክሲዮን ማህበር ነዉ፡፡
4. **“ቦርድ”** ማለት የልማት ድርጅቶችን የሥራ እንቅስቃሴ በበላይነት እንዲመራ የሚቋቋም የልማት ድርጅት ቦርድ ነው፡፡
5. **“ጠቅላላ ሀብት”** ማለት ሁሉም የማይንቀሳቀስና የሚንቀሳቀስ ንብረት፣ ተሰብሳቢ ሀብት፣ ጥሬ ገንዘብ፣ የባንክ ሂሳብ፣ የልማት ድርጅቶች የማይዳሰሱ ሀብቶች፣ የአገልግሎት ክፍያዎች እና ሌሎች እዳዎችን ያጠቃልላል፡፡
6. **“ጠቅላላ የተጣራ ሀብት”** ማለት ከጠቅላላ ሀብት የአጭር ግዜ ዕዳዎች፣ የረጅም ግዜ ዕዳዎች እና ሌሎች ዕዳዎች ተቀንሶ የሚገኝ ሀብት ነዉ፡፡
7. **“ካፒታል”** ማለት አንድ የልማት ድርጅት በሚመሠረትበት ጊዜና ከዚያ በኋላ በመንግሥት የሚመደብለት ጠቅላላ የተጣራ ሀብት በተመደበበት ጊዜ ያለው ዋጋ ነው፡፡

8. **“Buuxantino Tirfe”** yaa bajeetete diri giddo eote womaashshinna wolootu addi addi batooshshubbanni afantanno addi addi fulo, looso ha’risate, damoozaho, seeru garinni fulo assinoonni shallagubba, akkallete xeishsha hattono qallonna taakise baanteenna gattanno shallagooti.

9. **“Mootimmate Tirfe Qeecha”** yaa buuxamino tirfinni seeru riserve shallago xeinseenna mootimmate gatanno qeechaati.

10. **“Mancho”** yaa kalaqamu mancho woy seerunni mannimmate qoosso uynoonnisi bisooti.

11. Tenne wodho giddo mitte koo-teemmanni xawinsoonnihu wole koo-teemmano hanafanno.

3. **<u>Wodhi-woro</u>**

Biilloonyu latishshu uurrinshubbara assanno ayee irkonna ha’runsonna qorqorshshu, xanbenna taalloonye, loosu gumaamimmanna jeefisiisate dhuka dhabbachishate, yannittenna fulo ajishshanno, loosu qinaanbe roorenka bowirsitannonna xa’mamooshshe buuxisiissanno wodhi-woro aana illachishshinnota ikka noose.

8. **“የተጣራ ትርፍ”** ማለት በበጀት ዓመቱ ውስጥ ከገቢ ገንዘብና ከሌሎች ልዩ ልዩ ክፍያዎች ከሚገኙት ልዩ ልዩ ወጪዎች፣ ለሥራ ማስኬጃ፣ ደመወዝ፣ በሕጉ መሠረት ወጪ የተደረጉ ሂሳቦች፣ የእርጅና ቅናሽ ግምት እንዲሁም ወለድና ታክስ ተከፍሎ የሚቀረው ሂሳብ ነው፡፡

9. **“የመንግሥት የትርፍ ድርሻ”** ማለት ከተጣራ ትርፍ ሕጋዊ የመጠባበቂያ ሂሳብ ተቀንሶ ለመንግሥት የሚቀር ድርሻ ነው፡፡

10. **“ሰው”** ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም የሕግ ሰውነት የተሰጠው አካል ነው፡፡

11. በዚህ ደንብ ውስጥ በአንድ ጾታ የተገለጸው ሌላኛዉንም ጾታ ያካትታል፡፡

3. **<u>መርህ</u>**

ባለስልጣኑ ለልማት ድርጅቶች የሚያደርገው ማንኛውም ድጋፍ ፤ክትትልና ቁጥጥር ግልጽነት እና ፍትሃዊነት፤ የሥራ ውጤታማነት እና የማስፈጸም አቅምን የመጨመር፤ ዘመናዊ እና ወጪ ቆጣቢ፤ የሥራ ቅንጅትን በበለጠ የሚያጎለብት፤ እና ተጠያቂነትን የሚያረጋግጥ መርሆዎች ላይ ያተኮረ መሆን አለበት፡፡

## GAFA LAME

## HEXXO, TANTANO, BIILLOONYENNA LOOSU QEECHA

**4. Hexxo**

Biilloonyu hexxo:-

1. Latishshu uurrinshubba massagooshshenna gashshoote ha'runsatenni; yannitte korporeetete gashshootenna korporeetete faynaanse amurate diriirsatenni hattono loosu aana hosase ha'runsatenni latishshu uurrinshubba gumaamma; heewisamaanonna tirfaamma ikkitanno gede assate;
2. Mootimma latishshu uurrinshubba aana noose qorqoratenna massagooshshe aate qeechase badino garinni loosu aana hosiissanno assatenni qoqqowu mootimma latishshu uurrinshubba aana noose annimmate qoosso agarsiisate;
3. Mootimmate latishshu Poolisenna latishshu uurrinshubba loosu ha'rinsho mereero heedhanno waaxamme lifixisatenni qoqqowunnita miinju lopho buuxisate.

**5. Qara Loosu Mine**

Biillonyunnihu qaru loosu mini Hawaasi Quchuma ikke hasiishshisi garinni qoqqowu giddo ayee baycho sinu loosu mine uurrisara dandaanno.



## ክፍል ሁለት

## ዓላማ፤ አደረጃጀት፤ ሥልጣንና ተግባር

**4. ዓላማ**

የባለሥልጣኑ ዓላማ፡-

1. የልማት ድርጅቶቹን አመራርና አስተዳደር በመከታተል፤ ዘመናዊ የኮርፖሬት አስተዳደርና ፋይናንስ ሥርዓት በመዘርጋት እንዲሁም ሥራ ላይ መዋሉን በመከታተል የልማት ድርጅቶች ውጤታማ፤ ተወዳዳሪና አትራፊ እንዲሆኑ ማድረግ፤
2. መንግሥት በልማት ድርጅቶቹ ላይ ያለውን ተቆጣጣሪነት እና የአመራር ሰጪነት ሚናን በለየ መልኩ መተግበሩን በማረጋገጥ የክልሉ መንግስት በልማት ድርጅቶች ላይ ያለውን የባለቤትነት መብት ማስከበር፤
3. በመንግሥት የልማት ፖሊሲ እና በልማት ድርጅቶች ስምሪት መካከል የሚኖረውን ቅንጅት በማሳለጥ የክልሉን የኢኮኖሚ ዕድገት ማረጋገጥ ናቸው፡፡

**5. ዋና መሥሪያ ቤት**

የባለሥልጣኑ ዋና መሥሪያ ቤት ሐዋሳ ከተማ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ በማናቸውም የክልሉ አካባቢዎች ቅርንጫፍ ሊያቋቁም ይችላል፡፡

**6. Biilloonyu Tantano**

Biilloonyeho:-

1. Qoqqowu prezidantichi mootoonsannori Qaru Dayrekiterenna hasiishshishi garinni Layinki Dayrekiterooti;
2. Loosoho hasiissanno wole loosaasine heedhannosi.

**7. Biilloonyu Biilloonyenna Loosu Qeecha**

Biiloonyeho aantete worroonni biillonyinna loosu qeechi hee’rannosi.

1. Latishshu uurrinshubba poolisetenna istiraatejike hedo burqisanno; kajjituro loosu aana hossanno gede assanno;
2. Latishshu uurrinshubba boordete gambasinchonna miilla noonsa akatoomi, ogimma, rosichonna dandoo garinni file somantanno gede qoqqowu prezidantichira shiqishanno; loosu jeefishshansa ha’runsanno; seeru garinni loosu aaninni ka’anno gede qoqqowu prezidantichira hedo shiqishanno;
3. Wo’munni wo’ma mootimma akisyoone amaddino aksiyoonete maamarira dayrekiterootu boorde miilla file somantanno gede qoqqowu prezidaantichira shiqishanno; loosu jeefishshansa ha’runsanno; seeru garinni loosu aaninni ka’anno gede qoqqowu prezidaantichira hedo shiqishanno;

**6. የባለሥልጣኑ አደረጃጀት**

ባለሥልጣኑ:-

1. በክልሉ ርዕሰ መስተዳድር የሚሾሙ፣ዋና ዳይሬክተር እና እንደአስፈላጊነቱ ምክትል ዳይሮክተሮች ይኖሩታል፡፡
2. ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች ሠራተኞች ይኖሩታል፡፡

**7. የባለሥልጣኑ ሥልጣንና ተግባር**

ባለሥልጣኑ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡፡

1. የልማት ድርጅቶች የፖሊሲና የስትራቴጂ ሀሳቦችን ያመነጫል ሲፀድቁም ስራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል ፤
2. የልማት ድርጅቶችን ቦርድ ሰብሳቢ እና አባላትን ባላቸው ስነምግባር፣ ሙያ፣ ልምድና ችሎታ መሠረት መልምሎ እንዲሰየሙ ለክልሉ ፕሬዝዳንት ያቀርባል፤ የስራ አፈፃፀማቸውን ይከታተላል፤በሕግ አግባብ ከሥራ እንዲሰናበቱ ለክልሉ ፕሬዝዳንት ሀሳብ ያቀርባል፤
3. መንግሥት ሙሉ በሙሉ የአክሲዮን ድርሻ በያዘባቸው አክስዮን ማህበራት ውስጥ መንግሥትን የሚወክሉ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት መልምሎ እንዲሰየሙ ለክልሉ ፕሬዝዳንት ያቀርባል፤ የስራ አፈፃፀማቸውን ይከታተላል፤በሕግ አግባብ ከሥራ እንዲሰናበቱ ለክልሉ ፕሬዝዳንት ሀሳብ ያቀርባል፤

4. Mootimma rooriiydi akisyoonete qeechi noose aksiyoonete maamari giddo mootimma lekkissanno dayrekiterootu boorde miilla file qoqqowu prezidaantichira shiqishanno; sumiimme afidhuro uurrinshate xaphooma songora shiqishe doorantanno gede assanno; loosu jeefishshansa ha'runsanno; xaphoomu songo seeru garinni loosu iiminni kayissanno gede assiisanno.
5. Latishshu uurrinshubba istiraateejikenna diru mixo mixi'ransa buuxanno, kaajjishanno, jeefishshansa qorqoranno, ha'runsanno, keenanno, taashshate qaafo adhanno;
6. Latishshu uurrinshubba shallago Qoqqowu Qara Odiite Loosu Mini qorqoranno gede assanno; gobbaaydi odiitere somanno; gobbaaydi odiite rippoorte kaajjishanno, odiitete gumi garinni taashshote qaafo adhamase ha'runsanno;
7. Latishshu uurrinshubba jeefishshinna heewisaanchimma woyyitanno assate yannitte korporeetete gashshootenna faynaanse gashshooti amuraate diriirsanno, tittirsha biddissunni murranni.
8. Latishshu uurrinshubba kaapitaale lexxitanno woy ajjanno gede murote hedo jeefisiisaanote amaale minira shiqishanno, fajjiniro loosu aana hosiisanno;
9. Latishshu uurrinshubba dandoo, loosu rosichinna egenno noonsa mannootinni massagantanno amuraate diriirsanno, loosu aana hosase buuxanno;

4. መንግሥት አብላጫ የአክሲዮን ድርሻ በያዘባቸው አክስዮን ማህበር ውስጥ መንግሥትን የሚወክሉ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት በመምረጥ ለክልሉ ፕሬዝዳንት ያቀርባል፤ ይሁንታ ሲያገኙ ለድርጅቱ ጠቅላላ ጉባኤ በማቅረብ እንዲመረጡ ያደርጋል፤የስራ አፈፃፀማቸውን ይከታተላል፤ በሕግ አግባብ በጠቅላላ ጉባኤው ከስራ እንዲያሰናበቱ ያስደርጋል፤
5. የልማት ድርጅቶች ስትራቴጂክና ዓመታዊ ዕቅድ ማቀዳቸውን ያረጋግጣል፤ ያፀድቃል፤ አፈፃፀማቸውን ይቆጣጠራል፤ ይከታተላል፤ ይገመግማል፤ የማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል፤
6. የልማት ድርጀቶችን ሂሳብ በክልሉ ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት እንዲመረመር ያደርጋል፤ የውጪ ኦዲተር ይሰይማል፤ የውጪ ኦዲት ሪፖርቶችን ያፀድቃል፤ በኦዲት ግኝቶች ላይ የእርምት እርምጃ መወሰዱን ይከታተላል፤
7. የልማት ድርጅቶች አፈፃፀም እና ተወዳዳሪነት እንዲሻሻል ለማድረግ ዘመናዊ የኮርፖሬት አስተዳደርና ፋይናንስ አስተዳደር ሥርዓት ይዘረጋል፤ ዝርዝሩ በመመሪያ ይወሰናል፤
8. የልማት ድርጅቶችን ካፒታል እንዲጨምር ወይም እንዲቀንስ ምክረ ሃሳብ ለመስተዳድር ምክር ቤት ያቀርባል፤ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፤
9. የልማት ድርጅቶች ችሎታ፤ ልምድ እና ዕውቀት ባላቸው ሰዎች የሚመሩበትን ሥርዓት ይዘረጋል፤ ተግባራዊነቱን ያረጋግጣል፤

10. Hasiishshisi garinni latishshu uurrinshubba hallanyunniwa soorrantanno, karsantanno, hi’rantanno, beehantanno woy diigantanno gede jeefisiisaanote amaale minira murote hedo shiqishanno, kaajjituro jeefishsha ha’runsanno ,jeefisiisanno;

11. Tirfete qeechi beehaachi amuraate qixxeessanno, buuxantino tirfe mittu mittunku baajeetete dirinni latishshu uurinshubbanni mootimmate baantanni tirfi qeechi baatooshshi bikkita murote hedo jefisiisaanote amaale minira shiqishanno, gumulliro loosu aana hosase ha’runsanno;

12. Latishshu uurrinshubba shallago mazigawunni sarraza lainohunni hasiissanno buuxo assatenni jefisiisaanote amaale minira murote hedo shiqishanno, jeefishsha ha’runsanno;

13. Latishshu uurrinshubba haranchonna seeda yanna liqoo faynaansete uurinshubbanni afidhanno gara xiinxallatenni loosu amuraate diriirsanno, loosu aana hosasi ha’runsanno;

14. Latishshu uurrinshubba faynaansete horoonsishsha, liqoo adhatenna qolate gara harunsanno;

15. Latishshu uurrinsha fajjinoonni kaapitaale garimma noosi seerira worroonni yanna giddo wo’munni wo’ma baatante gooffanno assanno, ha’runsanno, rizervete shallagubba

10.እንደ አስፈላጊነቱ የልማት ድርጅቶች ወደ ግል እንዲዛወሩ፣ ከሌላ ድርጅት ጋር እንዲዋሃዱ፤ እንዲሸጡ፣ እንዲከፈሉ ወይም እንዲፈርሱ ለመስተዳድር ምክር ቤት ምክረ ሃሳብ ያቀርባል፤ ሲፀድቅም ተፈፃሚነቱን ይከታተላል፤ ያስፈፅማል፤

11.የትርፍ ድርሻ ክፍፍል ሥርዓት ያዘጋጃል፤ ከተጣራ ትርፍ በየበጀት ዓመቱ ከልማት ድርጅቶች ለመንግሥት ስለሚከፈል የትርፍ ድርሻ ክፍያ መጠን ለመስተዳድር ምክር ቤት ምክረ ሃሳብ ያቀርባል፤ሲወሰንም ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤

12.የልማት ድርጅቶች ሂሳብ ከመዝገብ መሰረዝን በሚመለከት ተገቢውን ማጣራት በማድረግ ለመስተዳድር ምክር ቤት ምክረ ሃሳብ ያቀርባል፤ አፈፃፀሙን ይከታተላል፤

13.የልማት ድርጅቶች የአጭር እና የረጅም ጊዜ ብድር ከፋይናንስ ተቋማት የሚያገኙበትን የአሰራር ስርዓት አጥንቶ ይዘረጋል፤ ተግባራዊነቱንም ይከታተላል፤

14.የልማት ድርጅቶችን የፋይናንስ አጠቃቀማቸውን፤ የብድር አወሳሰድና አመላለሳቸውን ይከታተላል፤

15.የልማት ድርጅቱን የተፈቀደ ካፒታል አግባብ ባለው ሕግ በተመለከተው ጊዜ ውስጥ በሙሉ ተከፍሎ እንዲያልቅ ያደርጋል፤ ይከታተላል፤ የመጠባበቂያ

amadantanno woy mootimma womaashsha gaantanno gede jefisiisaanote amaale minira murote hedo shiqishanno, gumulliro loosu aana hossanno gede assanno;

16. Latishshu uurrinshubba xiinxallotenna kalaqate loosira ikkado baajeette gaantanno gede hattono xiinxallonna kalanqoonni gumi la’’annosi bisira tuqinsanni gara injeessanno;
17. Latishshu uurrinshubba jeefishsha leellishshanno taje tantananno, fatilanno, tuqisanno;
18. Latishshu uurrinshubba qaru loosu ha’risaanchinna layinki loosu ha’risaano qixirenna loosunni kaysate gumulo uurinshubbate bordenni shiqquro buuxe pirezidaantichaho hedo shiqishatenni sumiimme afidhuro kaajjishanno;
19. Latishshu uurrinshubba rosicho sooridhanno bare qixxeessanno, uurinshubbannita massagaanote dhuka lossate dandiisiissanno qajeelshuwa uuynanni gara injeessanno;
20. Latishshu uurinshubba giddo mootimma nooseta annimmate qoosso ayirrisiisate hasiissanno loossa loosate dandisiissanno loosu amuraate diriirsanno;
21. Latishshu uurrinshubba yaaddote loosi massagooshshi amuraate qixxeessanno, keenotenna jawaachishshu jeefishshi loosi amuraate diriirsanno;

ሂሳቦች እንዲያዙ ወይም ከመንግሥት ገንዘብ እንዲመደብ ለመስተዳድር ምክር ቤት ምክረ ሀሳብ ያቀርባል ሲወሰንም ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል፤

16. የልማት ድርጅቶች ለምርምር እና ለፈጠራ በቂ በጀት እንዲመድቡ እንዲሁም የተገኘውን የምርምር እና የፈጠራ ውጤት ለሚመለከተው አካል እንዲያሰራጩ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤
17. የልማት ድርጅቶችን አፈፃፀም የሚያሳይ የመረጃ ሥርዓት ያደራጃል፤ ይተነትናል ያሰራጫል፤
18. የልማት ድርጅቶች ዋና ሥራ አስኪያጅ እና ምክትል ስራ አስኪያጆች ቅጥር እና ስንብት ውሳኔ ከልማት ድርጅቶች ቦርድ ሲቀርብለት መርምሮ ለክልሉ ፕሬዝዳንት ሀሳብ ያቀርባል ይሁንታ ሲያገኝ ያፀድቃል፤
19. የልማት ድርጅቶች ተሞክሮ የሚለዋወጡበትን መድረክ ያዘጋጃል፣ የድርጅቶቹን የአመራር አቅም ለማሳደግ የሚያስችሉ ሥልጠናዎች እንዲሰጡ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤
20. በልማት ድርጅቶች ውስጥ መንግሥት ያለውን የባለቤትነት መብት ለማስከበር የሚያስፈልጉ ተግባራትን ለማከናወን የሚያስችል የአሠራር ሥርዓት ይዘረጋል፤
21. የልማት ድርጅቶችን የሥጋት ሥራ አመራር ሥርዓት ያዘጋጃል፤ የግምገማና የማበረታቻ አፈፃፀም አሠራር ሥርዓት ይዘረጋል፤

22. Latishshu uurrinshubba loossa mootimmate latishshu poolise ledo sumuu yitinota ikkitanno gede la’annosi bisi ledo halamatenni loosanno;
23. Latishshu uurrinshubba addi garinni tirfensa horonsidhanno woy halashshate loossara hosiisate dandisiissannonsa loosu amuraate diriirsanno;
24. Latishshu uurrinshubba kisaaru xaadinsaro buicho xiinxallote badatenni gumaamo ikkino fulo ajishate amuraate qixxeese jefisiisaanote amaale minira shiqishanno, gumulliro loosu aana hosasi ha’runsanno;
25. Latishshu uurrinshubba faynaansete loosi amuraate diriirsanno, loosu aana hosasi ha’runsanno;
26. Haaro latishshu uurrinshubba uurritanno gara xiinxallo assatenni jefisiisaanote amaale minira murote hedo shiqishanno, gumullirono uurrisate ha’rinsho massaganno;
27. Mootimma aksiyoone amaddino aksiyoonete maamarra giddo noota mootimmate horo la’anno hajubba aana mootimma amaalanno;
28. Latishshu uurrinshubba boordete miilla loosu waagi baatooshshe, loosu harisaanonna loosaasinete aganu baatooshshenna addi addi horo xiinxallo assinanni damatte hanqafaancho diriirsanno; jeefishsha harunsanno;

22. የልማት ድርጅቶች ተግባራት ከመንግሥት የልማት ፖሊሲዎች ጋር የተጣጣመ እንዲሆን ከሚመለከተው አካል ጋር በትብብር ይሰራል፤
23. የልማት ድርጅቶች በልዩ ሁኔታ ትርፋቸውን እንዲጠቀሙ ወይም ለማስፋፍያ እንዲያውሉ የሚያስችላቸውን የአሰራር ስርዓት ይዘረጋል፤ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤
24. የልማት ድርጅቶች ኪሳራ ሲያጋጥማቸው ምንጩን በጥናት በመለየት፤ አዋጭ የሆነ የወጪ ቅነሳ ሥርዓት እና ተጨማሪ ገቢ አማራጭ አዘጋጅቶ ለመስተዳድር ምክር ቤት ያቀርባል፤ ሲወሰንም ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤
25. የልማት ድርጅቶቹ የፋይናንስ አሠራር ሥርዓት ይዘረጋል፤ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤
26. አዳዲስ የልማት ድርጅቶች ስለሚቋቋሙበት ሁኔታ ጥናት በማድረግ ለመስተዳድር ምክር ቤት የውሳኔ ሀሳብ ያቀርባል፤ ሲወሰንም የማቋቋም ሂደቱን ይመራል፤
27. መንግሥት የአክሲዮን ድርሻ በያዘባቸው አክሲዮን ማህበራት ውስጥ ያለውን የመንግሥት ጥቅም በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ መንግሥትን ያማክራል፤
28. የቦርድ አባላት የስራ ዋጋ፣ የሥራ አስኪያጆች እና የሠራተኞች ደመወዝና ጥቅማ ጥቅም ጥናት የሚደረግበትን መሠረታዊ ማዕቀፍ ይዘረጋል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፤

29. Latishshu uurrinshubba dagoomitte owaante gadachonsa fultanno gede assanno; jeefishsha harunsanno;

30. Latishshu uurrinshubba yannitte akatansa ha’runsanno; tirote faasho woranno;

31. Qoqqowu latishshu fande uurritanno gede qoqqowu jeefisiisaanote amaale minira hedo shiqishanno; kaajjituro latishshu fande uurritanno harinsho massaganno;

32. Latishshu uurrinshubba mootimmate tirfete qeecha latishshu fandera eo assitanno gede assanno; ha’runsanno.

33. Latishshu uurrinshubba mixote jeefishsha pirogiraamete garinni keenanno, filiqishsha qolanno yanna yannatenni irkonna ha’runso hattono qorqorsha assanno.

34. Latishshu uurrinshubba hirotenna jajju gashshooti amanyooti xawado, fulo ajishinohanna seeda yanna horo kaima ssinoha ikkasi buuxanno, qorqoranno

35. Biilloonyu hexxo jefisiisate hasiissanno wolootta loossa loosanno.

**8. <u>Qaru Dayrekitere Biilloonyenna Loosu Qeecha</u>**

Qaru Dayrekiterera aantete worroonni biilloonyinna loosu qeechi hee’rannosi:-

1. Biilloonyu qara loosu jeefisiisaancho

29. የልማት ድርጅቶች ለማህበረሰቡ ማህበራዊ አገልግሎት የመስጠት ግዴታቸውን እንዲወጡ ያደርጋል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፤

30. የልማት ድርጅቶች ወቅታዊ ሁኔታዎችን ይከታተላል፤ የመፍትሄ አቅጣጫ ያስቀምጣል፣

31. የክልሉ የልማት ፈንድ እንዲቋቋም ምክረ-ሃሳብ ለመስተዳድር ምክር ቤት ያቀርባል፤ ሲወሰንም ሂደቱን ይመራል፤

32. የልማት ድርጅቶች የመንግስት የትርፍ ድርሻ ከተጣራ ትርፍ ህጋዊ የመጠባበቂያ ሂሳብ ተቀንሶ ወደ ልማት ፈንድ ገቢ ማድረጋቸዉን ይከታተላል፤

33. የልማት ድርጅቶች የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት በመርሀ ግብር መሠረት ይገመግማል፤ ግብረ-መልስ ይሰጣል፣ በየወቅቱ ክትትልና ድጋፍ እንድሁም ቁጥጥር ያደርጋል፣

34. የልማት ድርጅቶች የግዥና ንብረት አስተዳደር ሥርዓት ግልፀኝነትን፣ ወጪ ቆጣቢነትን እና ዘላቂ ጠቀሜታን መሠረት ያደረገ መሆኑን ያጣራል፣ ይቆጣጠራል፣

35. የባለስልጣኑን ዓላማ ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

**8. <u>የዋና ዳይሬክተር ሥልጣንና ተግባር፤</u>**

ዋና ዳይሬክተሩ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. የባለስልጣኑ ዋና ሥራ አስፈፃሚ በመሆን

ikkatenni biilloonyu loossa massaganno; gashshanno.

2. Konni quwi cinaanchu quwi (1) xaphoomu woro noo gedeenni heedheenna qaru dayrekitere:-

a. Tenne wodho quwa 7 worroonni biilloonyu biilloonyenna loosu qeecha loosu aana hosiisano;

b. Biilloonyunnita tantanote taqqa qixxeessanno;

c. Biilloonyunnita mannu wolqa hasatto xiinxallote badatenni loosaasine qaxaranno, gashshanno;

d. Biilloonyunnita istirateejikenna dirunnita loosunna baajeetete mixo dirunnita loosunna bajeettete mixo qixxeessanno, kaajjituro loosu aana hosiisanno;

e. Biilloonyu loosu pirogiraamenna bajeette garinni baatooshshubba jeefisanno;

f. Sayikki bisi ledo assinanni xaadooshshubbara biilloonye lekkisanno;

g. Biilloonyunnita jeefishshu rippoorte qoqqowu jeefisiisaanote amaale miniranna qoqqowu amaale minira shiqishanno;

3. Loosu lifinxeranna rankera hasiisannobikkini biilloonyenna loosu qeechasi beehe layinki dayrekitereranna woloota biilloonyu loosaasinera riqiwotenni saysara dandaanno.

የባለስልጣኑን ሥራዎች ይመራል፤ ያስተዳድራል፤

2. የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ዳይሬክተሩ:-

ሀ. በዚህ ደንብ በአንቀፅ 7 የተመለከቱትን የባለስልጣኑን ሥልጣንና ተግባራት ሥራ ላይ ያውላል፤

ለ. የባለሥልጣኑን የአደረጃጀት መዋቅር ያዘጋጃል፤

ሐ. የባለሥልጣኑን የሰው ሃይል ፍላጎት በጥናት በመለየት ሠራተኞችን ይቀጥራል፤ ያስተዳደራል፤

መ. የባለሥልጣኑን ስትራቴጂያዊ እና ዓመታዊ የሥራ እና የበጀት ዕቅድ ያዘጋጃል፤ ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

ሠ. የባለስልጣኑ የሥራ ፕሮግራምና በጀት መሠረት ክፍያዎችን ይፈጽማል፤

ረ. ከሶስተኛ ወገን ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ባለሥልጣኑን ይወክላል፤

ሰ. የባለሥልጣኑን የሥራ አፈፃፀም ሪፖርት ለመስተዳድር ምክር ቤት እና ለክልሉ ምክር ቤት ያቀርባል፤

3. ለሥራ ቅልጥፍና በሚያስፈልግ መጠን ሥልጣንና ተግባሩን በከፊል ለምክትል ዳይሬክተሩ እና ለሌሎች የባለሥልጣኑ

**9. Layinki Dayrekitere Biilloonyenna Loosu Qeecha**

Layinki dayrekitere qaru dayrekitere hundaancho ikke aantete worroonni biilloonyinna loosu qeechi hee’rannosi:-

1. Handaaraho uynanninsa rosantino loossa loossanno;
2. Biilloonyu looso mixi’ratenni, tantanatenni, massagatenninna qineessatenni qara dayrekitericha kaa’lanno;
3. Qaru Dayrekitere hee’rannokki yannara woy looso loosate loososi loosa dandaannokki yannara lekkise loosanno;
4. Qaru Dayrekitere bade aannosita woloota loossa loosanno.

**10.** Biillonyu kunni woroonni noo latishshu urinshubba irkisannoha, harunsannohanna qorqorannoha ikkanna qoqqowu mootimma gumulonni biilloonyu hundaanni galtanno gede lendanni uurrinshubbanna albillicho uurritanno latishshu uurrinshubba qorqoranno.

1. Konsitrakishiinete Loossa Korporeshiine,
2. Sidaamu Lophote Korporeshiine,
3. Sidaamu Dizaynenna Ijaaru Qorqorshi Interprayze,
4. Furra Lophotenna Xiinxallote Uurrinsha;
5. Industirete Paarkuwa Korporeshiine,
6. Hayyoolle Rosu Projekite,
7. Adaare Lukkuwu Ceo Interprayze

ሠራተኞች በውክልና ሊያስተላልፍ ይችላል፡፡

**9. የምክትል ዳይሬክተር ሥልጣንና ተግባር**

ምክትል ዳይሬክተሩ ተጠሪነቱ ለዋና ዳይሬክተር ሆኖ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. በዘርፍ የሚሰጠውን መደበኛ ሥራዎች ያከናውናል፤
2. የባለሥልጣኑን ሥራ በማቀድ፣ በማደራጀት፣ በመምራትና በማስተባበር ዋና ዳይሬክተሩን ይረዳል፤
3. ዋና ዳይሬክተሩ በማይኖርበት ጊዜ ወይም ሥራውን ማከናወን በማይችልበት ጊዜ ተክቶ ይሠራል፤
4. በዋና ዳይሬክተሩ ተለይተው የሚሰጡ ሌሎች ተግባሮችን ያከናውናል፡፡

10. ባለስልጣኑ ከዚህ በታች የተዘረዘሩ የልማት ድርጅቶችን የሚደግፍ፤ የሚከታተልና የሚቆጣጠር ሆኖ በክልሉ መንግስት ተወስነው በልማት ድርጅቶች የሚካተቱ ተጨማሪ ድርጅቶች እንዲሁም ወደ ፊት የሚቋቋሙ የመንግስት የልማት ድርጅቶችን የሚቆጣጠር ይሆናል፡፡

1. የሲዳማ ኮንስትራክሽን ሥራዎች ኮርፖሬሽን፣
2. የሲዳማ ልማት ኮርፖሬሽን፣
3. የሲዳማ ዲዛይንና ግንባታ ቁጥጥር ኢንተርፕራይዝ፣
4. ፉራ ጥናትና ምርምር ተቋም፣
5. ኢንዱስትሪ ፓርኮች ኮርፖሬሽን፣
6. ሀዮሌ ትምህርት ፕሮጀክት፣
7. አዳሬ ዶሮ እርባታ ኢንተርፕራይዝ፣

8. Hawaasi Daabbotenna Bulleete Interprayze

## GAFA SASE

### Addi Addi Woro

**11. Bajeette**

Biilloonyu bajeette mootimmatenni gaammanni

**12. Biilloonyu Shallagote Taje**

Biilloonyu:-

1. Wo'manna halaalaancho shallagote taje amadanno;
2. Shallagote tajenna womaashsha amaddino sanade qara odiiterenni woy qara odiitere lekkisino odiiterenni diru dirunkunni qorqorantanno.

**13. Loosu Aana Hossannokki Seerubba**

Tenne wodho ledo kiphantanno ayee wodho, biddissi woy rosamino assooti tenne wodhonni hanqafantino hajubbara jeefishshu dihee'rannosi.

**14. Biddissa Fushshate Biilloonye**

Biilloonyu wodho jeefisiisate hasiissanno biddisubba fushshara dandaanno.

**15. Wodho Loosu Aana Hossanno Yanna**

Tini wodho wonsini barrinni Badheessa 8/2017 M.D hanaffe kaajjitinota ikkitanno.

**Hawaasa, Badheessa 8/ 2017 M.D**

**Desta Ledamo**

**Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Pirezidanticha**

8. ሀዋሳ ዱቄትና ዳቦ ፋብሪካ፣

## ክፍል ሶስት

### ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**11. በጀት**

የባለስልጣኑ በጀት በመንግሥት ይመደባል፡

**12. የባለስልጣኑ የሂሳብ መዝገብ**

ባለስልጣኑ፡-

1. የተሟላና ትክክለኛ የሆነ የሂሳብ መዛግብት ይይዛል፤
2. የሂሳብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሠነዶች በዋና ኦዲተር ወይም ዋናው ኦዲተር በሚወክለው ኦዲተር በየዓመቱ ይመረመራል፡፡

**13. ተፈጻሚነት የማይኖራቸው ሕጎች**

ከዚህ ደንብ ጋር የሚቃረን ማናቸውም ደንብ፣ መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሠራር በዚህ ደንብ በተመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖራቸውም፡፡

**14. መመሪያ የማውጣት ሥልጣን**

ባለስልጣኑ ደንቡን ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

**15. ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ**

ይህ ደንብ ከፀደቀበት ከመጋቢት ቀን ፳፻፲፯ ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**ሀዋሳ፣ መጋቢት ፰ ቀን ፳፻፲፯ ዓ.ም**

**ደስታ ሌዳሞ**

**የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ርዕሰ መስተዳድር**